# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድ እና ትራንስፖርት ቢሮ
# የመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ፍጥነት ወሰን መመሪያ

---

## ቁጥር 39/2013

ጥቅምት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**


መግቢያ ..... 3

ክፍል አንድ ..... 3

ጠቅላላ ድንጋጌዎች ..... 3

1. አጭር ርዕስ ..... 3
2. ትርጓሜ ..... 3
3. የተፈፃሚነት ወሰን ..... 5
4. የጾታ አገላለፅ ..... 5

ክፍል ሁለት ..... 6

የፍጥነት ወሰን ..... 6

5. የፍጥነት ወሰን አወሳሰን አጠቃላይ መሰረታዊ መረሆዎች ..... 6
6. መደበኛ የፍጥነት ወሰን ..... 7
7. ልዩ የፍጥነት ወሰን ..... 7

ክፍል ሦስት ..... 8

የቅጣት አፈፃፀም ..... 8

8. ቅጣት ..... 8
9. የተሽከርካሪ ባለንብረት ኃላፊነት ..... 8
10. የማስፈፀም ስልጣን ..... 8
11. የመተባበር ግዴታ ..... 8
12. የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር ..... 8
13. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች ..... 9
14. የሚፀናበት ጊዜ ..... 9

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ በትራፊክ አደጋ ምክንያት በእግ ረኞች ላይ እየደረሰ የሚገኘው ከፍተኛ የሆነ የሞት፣ የአካል መጉደል እና የህሊና (የሞራል) ጉዳት ለመቀነስ ልዩ ትኩረት በመስጠት አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ የታመነበት በመሆኑ፤

እየጨመረ የሚገኘው የትራፊክ አደጋ እና በዚህም ምክንያት እየደረሰ ያለውን ሰብአዊ ጉዳትና ቁሳዊ ኪሳራ ለመከላከል ታስቦ የተቀረጸውን የመንገድ ደህንነት ስትራቴጅ ሰነድ ታሳቢ ያደረገ እርምጃ ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ከተሽከርካሪ ፍጥነት ጋር በተያያዘ የሚደርሱ የትራፊክ አደጋዎች በየጊዜው እየጨመሩ የሚገኙ መሆኑን በጥናት በመረጋገጡ እና አደጋዎችን መቀነስ ታሳቢ ያደረገ የፍጥነት ወሰን መደንገግ በማስፈለጉ፤

የከተማችን ሁለተናዊ ዕድገት በተለይ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የእንቅስቃሴ መስፋፋት እንዲሁም የተሻሻሉ የመንገድ መሰረተ ልማቶችንና የዘመናዊ ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ግምት ውስጥ ያስገባ በባለሞተር ተሽከርካሪ እና በመንገዶች አይነትና ደረጃ የሚያገለግል እንደየሁኔታው በየጊዜው ሊከለስ የሚችል የፍጥነት ወሰን ሊኖር እንደሚገባ በመታመኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀፅ 9 ንዑስ ቁጥር 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን የአዲስ አበባ ከተማ የባለሞተር ተሽከርካሪ የመንገድ ፍጥነት ወሰን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ፍጥነት ወሰን መመሪያ ቁጥር 39/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡
2. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማለት ነው፡፡
3. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ማለት ነው፡፡
4. **"ኤጀንሲ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡
5. **"ቀለበት መንገድ"** ማለት ዋና አገልግሎቱ የትራፊክ እንቅስቃሴን ፈጣን ማድረግ የሆነ፣ በአንድ አቅጣጫ የውስጥ እና የውጭ መጋጋዣ መንገድ ያለው፣ እግረኛ እንዳያቋርጥ መከለያ ሊኖረው የሚችል፣ በከተማ ዙሪያ የሚገኝ እና ትራፊክ ወደ መሃል ከተማ ሳይገባ ወደ መዳረሻ እንዲጓዝ የሚያስችል መንገድ ማለት ነው፡፡

6. **"ዋና የከተማ ጎዳና"** ማለት የቀለበት መንገድን ሳይጨምር ዋና አገልግሎቱ ከፍተኛ ብዛት ያለውን ትራፊክ በፍጥነት ማስተናገድ የሚችል፣ ውስን የሆነ የመንገድ መጋጠሚያ ኖሮት ረዘም ያለ ርቀት ለማሽከርከር ታስቦ የተሰራ መንገድ ማለት ነው::

7. **"መለስተኛ የከተማ ጎዳና"** ማለት ደረጃው ከዋና የከተማ ጎዳና ያነሰ፣ አገልግሎቱ የትራፊክ እንቅስቃሴ ወደ ተለያየ አቅጣጫ ማከፋፈል የሆነ፣ በአጭር ርቀት ውስጥ ከሰብሳቢ እና ከመንደር ውስጥ መንገዶች ጋር በከፍተኛ ደረጃ ለማገናኘት ተብሎ የተሰራ መንገድ ማለት ነው::

8. **"ሰብሳቢ መንገድ"** ማለት አገልግሎቱ በዋናነት የትራፊክን እንቅስቃሴ ከመለስተኛ/ዋና ጎዳና ወደ መለስተኛ/ዋና ጎዳና ወይንም መለስተኛ ጎዳናን ከውስጥ ለውስጥ መንገድ ለማገናኘት ተብሎ የተሰራ መንገድ ማለት ነው::

9. **"የመንደር ውስጥ መንገድ"** ማለት በአብዛኛው ጊዜ ወደ ንብረት የሚደረግ የትራፊክ እንቅስቃሴን ለማካሄድ እንዲረዳ ተብሎ የተሰራ መንገድ ማለት ነው::

10. **"ባለሞተር ተሽከርካሪ"** ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ሐይል የሚንቀሳቀስ አውቶሞቢል፣ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ፣ ከባድ ተሽከርካሪ፣ ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ፣ ባለሁለት እግር ተሽከርካሪ ማለት ነው::

11. **"የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ"** ማለት ማንኛውንም አይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ተሳቢ ሊኖረው ይችላል::

12. **"የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ"** ማለት መንገደኞችን ለማመላለስ የሚያገለግል ባለሞተር ተሽከርካሪ ማለት ነው::

13. **"አውቶቡስ"** ማለት ከአስራ ስድስት መንገደኞች በላይ ማሳፈር የሚችል የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ማለት ነው::

14. **"አደጋ ሊያስከትል የሚችል ጭነት"** ማለት ማንኛውንም በሃገሪቱ ህግ አደጋን ሊያስከትል የሚችል ተብሎ የተመደበ ንጥረ ነገር ማለት ነው::

15. **"የተሽከርካሪ ማንሻ ተሽከርካሪ"** ማለት በተለያዩ መንገዶች ላይ በብልሽት ወይም በተለያዩ ምክንያት ቆመው ለትራፊክ እንቅስቃሴ እክል ሊፈጥሩ የሚችሉ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ማንሻ አገልግሎት የሚውል ባለሞተር ተሽከርካሪ ማለት ነው::

16. **"የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ"** ማለት የድንገተኛ አደጋ እርዳታ አገልግሎት ተግባርን ለመፈፀም በሚዘዋወርበት ወቅት ሳያቋርጥ ብልጭ ብልጭ የሚል ቀይ ወይም ሰማያዊ የመብራት ምልክት የሚያሳይ ወይም ለማስጠንቀቂያ ተስማሚ የሆነ የድምፅ ምልክት ወይም ደውል እያሰማ በግዳጅ ላይ ያለ አምቡላንስ፣ የመከላከያ ወይም የፖሊስ ሀይል እና የእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪ ነው::

17. **"ልዩ ተንቀሳቃሽ መሳሪያ"** ማለት ሰውን ወይንም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ሳይሆን፣ ለእርሻ፣ ለከብት እርባታ፣ ለመንገድ፣ ለህንጻ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማናቸውም ተመሳሳይ ሌላ ስራ የተሰራ ወይም ለዚሁ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው::

18. **"ተሳቢ"** ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ሃይል የሌለው ጎታች በሆነ ሌላ ባለሞትር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችል፣ ክብደቱ ጎታች ከሆነው ባለሞትር ተሽከርካሪ ላይ የማያልፍ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፡፡

19. **"ከባድ ተሽከርካሪ"** ማለት ከነጭነቱ በህግ የተፈቀደው ጠቅላላ ክብደት ሰባ አምስት ሽህ (75000) ኪሎ ግራም በላይ የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

20. **"ባለሁለት እግር ተሽከርካሪ (ባለሞተር ብስክሌት)"** ማለት በሁለት ጎማ የሚንቀሳቀስ ባለሞተር ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

21. **"ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ"** ማለት በሶስት ጎማ የሚንቀሳቀስ ባለሞተር ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

22. **"ቅድሚያ መስጠት"** ማለት የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪን የሚያሽከረክር አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ጊዜ ወይም በተለያዩ ህጎች አጀብ እንዲደረግላቸው የሚያስገድድ ተሽከርካሪዎች አጀብ ተደርጎላቸው በሚጓዙበት ጊዜ ምንም አይነት ችግር ሳይገጥመው ማሽከርከር እንዲችል መንገዱን ነጻ ማድረግ ማለት ነው፡፡

23. **"መደበኛ የፍጥነት ወሰን"** ማለት በማንኛውም የከተማዋ መንገድ ላይ አንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሊያሽከረክርው የሚፈቀድለት ከፍተኛው የተሽከርካሪ ፍጥነት ማለት ነው፡፡

24. **"ልዩ የፍጥነት ወሰን"** ማለት በማንኛውም የከተማዋ መንገድ ላይ በመደበኛ የፍጥነት ወሰን ከተፈቀደው የፍጥነት ወሰን ውጪ ኤጀንሲው በወሰነው የፍጥነት ወሰን መሰረት ዝቅ በማድረግ አንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ እንዲያሽከረክር የሚስገድድ የተሽከርካሪ ፍጥነት ማለት ነው፡፡

25. **"የትራፊክ ተቆጣጣሪ"** ማለት ማንኛውም የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠርና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር ስልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የተመደበ ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ወይም በኤጀንሲው የተመደበ የደንብ ማስከለበር እና ቁጥጥር ሰራተኛ ወይም ሌላ በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡

26. **"አሽከርካሪ"** ማለት በዚህ መመሪያ ባለሞተር ተሽከርካሪ ተብለው የሚታወቁትን ተሽከርካሪዎች የሚያሽከረክር ሰው ነው፡፡

27. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሰውነት ሙብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በማንኛውም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚተዳደሩ መንገዶች ላይ በሚሽከረከሩ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**4. የጾታ አገላለፅ**

ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የፍጥነት ወሰን

### 5. የፍጥነት ወሰን አወሳሰን አጠቃላይ መሰረታዊ መረሆዎች

5.1 ማንኛውም አሽከርካሪ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ላይ ትኩረት በመስጠትና በማመዛዘን ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም የከተማ መንገድ ላይ የሞተር ተሽከርካሪን ማሽከርከር የለበትም፡፡

ሀ. የመንገድ ንጣፍ (ዓይነት)፣ ስፋትና ጠቅላላ የመንገዱን ሁኔታ፤

ለ. መንገዱ የሚገኝበት የመሬት አቀማመጥ (ጠመዝማዛነት፣ ዳገታማነት እና ቁልቁለታማነት፣ ወዘተ)፤

ሐ. የመንገዱን የከባቢ የአየር ሁኔታ ማለትም ዝናብ፣ ጭጋግ ወይም ሌላ የተፈጥሮ ሁኔታ መኖር፤

መ. በመንገዱ አካባቢ ያለውን የህዝብ እንቅስቃሴና መጠን፤

ሠ. በመንገድ የሚገኙትን ወይም ይኖራል ተብሎ የሚገመቱትን የትራፊክ ፍሰት ሁኔታ፤

ረ. በመንገዱና በመንገዱ አከባቢ የሚገኙ የትራፊክ እንቅስቃሴ የሚያውኩ አዋኪ ነገሮች ማለትም የተዘጉ መተላለፊያዎች፣ ተበላሽተው የቆሙ ተሽከርካሪዎች፣ የወደቀ አለትና ሌላም መተላለፍን የሚያውክ መሰናከል መኖሩን፤

ሰ. በመንገዱ አከባቢ የሚገኙ የአገልገሎት መስጫ ተቋማት (የገበያ ማዕከል፣ ትምህርት ቤት፣ የሀይማኖት እና የጤና ተቋማት፣ ወዘተ) የሚገኙበት ሁኔታ፤

ሸ. የመንገድ መጋጣጠሚያዎች ወይም የእግረኞች ማቋረጫዎች ያሉበት ሁኔታ፤

ቀ. በመንገድ ላይ የሚካሄዱ ክዋኔዎች ማለትም የተፈቀዱ የንግድ ወይም መሰል ትርኢቶች፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች፣ ቦታ የተከለለላቸው ገበያዎች መኖራቸውን፣

በ. አሽከርካሪው በማንኛውም ጊዜ ተሽከርካሪውን በሙሉ እንዳይቆጣጠርና አደጋን በማያደርስ አኳኋን እንዳይነዳ የሚያውክ ማንኛውም ሁኔታ መኖሩን፣

5.2 ከዚህ በታች በአንቀፅ 6 የተመደበው የፍጥነት ወሰን ቢኖርም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5.1 የተጠቀሱት ሁኔታዎች ሲኖሩ ማንኛውም አሽከርካሪ ፍጥነቱን ቀንሶ ማሽከርከር ይኖርበታል፡፡

5.3 የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎችን ለማስቀደም ሲባል ማንኛውም አሽከርካሪ የተሽከርካሪውን ፍጥነት ከተፈቀደው በታች መቀነስ ወይም ማቆም ይኖርበታል፡፡

5.4 ማንኛውም አሽከርካሪ በከተማዋ መንገዶች ላይ ባለሞተር ተሽከርካሪን በሚያሽከርከርበት ጊዜ ድንገተኛ አደጋን ለመቋቋምና በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ 5.1 እስከ ንዑስ አንቀፅ 5.3 በተገለፁት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የትራፊክ እንቅስቃሴን በሚዘጋና በሚያግድ አዝጋሚ ፍጥነት ወይም በመንገድ ላይ ከተቀመጠ ዝቅተኛ የፍጥነት ወሰን በታች ማሽከርከር ወይም ፍጥነቱን በድንገት መቀነስ የለበትም፡፡ ፍጥነት በድንገት የመቀነስ ሀሳቡንም ጊዜውን የጠበቀና ግልፅ በሆነ ምልክት ማሳወቅ አለበት፡፡

5.5 በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ 5.1 እስከ ንዑስ አንቀፅ 5.4 በተገለፁት ሁኔታዎች ወይም አደጋ እንዳይደርስ በዝግታ ማሽከርከር አስፈላጊ ሲሆን ወይም አጠገቡ የሚንቀሳቀስ ትራፊክ ጋር ሲነፃፀር በዝግታ የሚነዳ ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ የመንገዱን የቀኝ ጠርዝ ይዞ መሄድ አለበት፡፡

## 6. መደበኛ የፍጥነት ወሰን

6.1 በከተማ ክልል ውስጥ የሚያሽከረክር ማንኛውም አሽከርካሪ በግልፅ በመንገዱ ላይ የሚታይ የተቀመጠ ልዩ የፍጥነት ወሰን የሚደነግግ የትራፊክ ምልክት ከሌለ በስተቀር ማንኛውንም የሞተር ተሽከርካሪ መደበኛ የፍጥነት ወሰን እንደሚከተለው ነው፡፡

6.1.1 የእግረኛ መንገድ በሌለበት የመንደር ውስጥ እና የሰብሳቢ መንገድ ላይ በሰዓት ከ15 ኪሎ ሜትር በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

6.1.2 የእግረኛ መንገድ ባለበት የመንደር ውስጥ እና የሰብሳቢ መንገድ ላይ በሰዓት ከ30 ኪሎ ሜትር በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

6.1.3 በመለስተኛ የከተማ ጎዳና ላይ በሰዓት ከ40 ኪ.ሜ. በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

6.1.4 በዋና የከተማ ጎዳና እና በቀለበት መንገድ የውጭኛው መተላለፊያ መስመር ላይ በሰዓት ከ50 ኪ.ሜ. በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

6.1.5 በቀለበት መንገድ የውስጠኛው መተላለፊያ መስመር ላይ በሰዓት ከ70 ኪ.ሜ. በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

6.1.6 የቀላል ባቡር የተዘረጋበትን መስመር ተከትሎ በሚገኝ ዋና የከተማ ጎዳና ላይ በሰዓት ከ40 ኪ.ሜ. በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

6.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6.1 የተመደበው የፍጥነት ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

6.2.1 አውቶቡስ፣ ከባድ ተሽከርካሪ፣ የተሽከርካሪ ማንሻ ተሽከርካሪ ወይም ባለሶስት እግር ተሽከርካሪን የሚያሽከረክር አሽከርካሪ በየትኛውም መንገድ ላይ በሰዓት ከ40 ኪ.ሜ. በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

6.2.2 አደጋ ሊያስከትል የሚችል ጭነት የጫነ ባለሞተር ተሽከርካሪና ማንኛውንም ዓይነት የልዩ ተንቀሳቃሽ መሳሪያ የሚያሽከረክር አሽከርካሪ በየትኛውም የከተማዋ መንገድ ላይ በሰዓት ከ30 ኪ.ሜ. በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

6.3 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6.1 እና 6.2 የተመደበው የፍጥነት ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም መንገድ ላይ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ የተቀመጠ የፍጥነት ወሰን ምልክት በማይኖርበት ጊዜ ማንኛውንም አይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚያሽከረክር አሽከርካሪ በሰዓት ከ40 ኪ.ሜ. በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

## 7. ልዩ የፍጥነት ወሰን

7.1 በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ለመንገድ ትራፊክ ደህንነት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በማንኛውም መንገድ ላይ የሚሽከረከር ማንኛውም አይነት የባለሞተር ተሽከርካሪ ከላይ በአንቀፅ 6 የተመደበውን የፍጥነት ወሰን መቀነስ አለበት፡፡

7.2 በየጊዜው በመንገድ ላይ ያለውን የትራፊክ ብዛት፣ የትራፊክ አደጋ ሁኔታ፣ የአካባቢ ሁኔታ፣ የመንገድ ሁኔታ በተለይም ትምህርት ቤቶችን ፣ ህዝብ የሚበዛባቸው የመኖሪያ እና የንግድ ቦታዎችን፣ የግንባታ ሥፍራዎችን በማጥናት ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቦታ፣ በሰዓትና በቀን በመወሰን ልዩ የፍጥነት ወሰን መመደብ ይችላል፡፡

7.3 የመንገዱን ሁኔታ፣ የመንገዱን ትራፊክ አደጋ ሪከርድ እና በመንገዱ ላይ የሚኖረውን የትራፊክ እንቅስቃሴ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመንገዱ ላይ ሊኖር የሚገባውን ዝቅተኛ የፍጥነት ወሰን እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 ላይ ከተቀመጠው አንደኛው የፍጥነት ወሰን ወደሌላኛ የፍጥነት ወሰን ወይም ከክልል ወደ አዲስ አበባ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ፍጥነታቸውን የሚያስተካክሉበት የመሸጋገሪያ የፍጥነት ወሰን ኤጀንሲው በጥናት መወሰን ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የቅጣት አፈፃፀም

8. **ቅጣት**

8.1 የዚህን መመሪያ ድንጋጌ የጣሰ ማንኛውም አሽከርካሪ አግባብነት ባለው ህግ ላይ የተቀመጠ ቅጣት እና የቅጣት አፈፃፀም መሠረት ይቀጣል፡፡

8.2 በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሰውን የፍጥነት ወሰን በማለፍ ባለሞተር ተሽከርካሪን ያሽከረከረ ማንኛውም አሽከርካሪ ሌላ ማንኛውንም የትራፊክ ደንብ በተመሳሳይ ጊዜ ተላልፎ ከተገኘ ለየጥፋቶቹ የተቀመጡት ቅጣቶች ድምር ይቀጣል፡፡

9. **የተሽከርካሪ ባለንብረት ኃላፊነት**

ማንኛውም አሽከርካሪ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ጥፋቶችን ፈፅሞ ያመለጠ ከሆነ የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለንብረት ጥፋት በተሰራበት ወቅት ማን ሲያሽከረክር እንደነበረ የማሳወቅ ሓላፊነት መውሰድ ወይም ጉዳዩ እስከሚጣራ ድረስ ጥፋት የተፈጸመበት ተሽከርካሪ በከተማ ውስጥ እንዳይንቀሳቀስ ሊታገድ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. **የማስፈፀም ስልጣን**

ኤጀንሲው ይህንን መመሪያ በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል ክትትል እንዲያደርግና የመንገድ ደረጃዎች፣ አይነቶችና የፍጥነት ወሰን አመላካች ምልክቶችን የመትከልና የማስታወቅ ስራ በዚህ መመሪያ ስልጣን ተሰቷል፡፡

11. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነትና መከበር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12. **የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር**

በሌሎች ህጎች የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የሚከተሉት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

12.1 የተሽከርካሪን ፍጥነት የመቆጣጠር ተግባር ለመፈጸም በማንኛውም ቦታ እና ሰዓት በከተማዋ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪ ሊያስቆም ይችላል፡፡

12.2 የተሽከርካሪዎች የፍጥነት መጠን በተለያዩ ዘዴዎች እና ቴክኖሎጂዎች ማለትም በራዳር፣ በፓትሮል ተሽከርካሪ/በሞተር ሳይክል የፍጥነት መለኪያ (ስፒዶሜትር) በመጠቀም ሊቆጣጠር ይችላል፡፡

**13. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**14. የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በቢሮ ኃላፊ ከተፈረመበት ከጥቅምት 02 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ጥቅምት 02 ቀን 2010 ዓ.ም

ሰለሞን ኪዳኔ ዘገየ (ዶ/ር)

የአዲስ አበባ ከተማ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ